የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ		
I. አጠቃላይ መግለጫ		
የመሥሪያ ቤቱ ስም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት
ጤና ጥበቃ ሚ/ር	የፊዚዮቴራፒ ሀኪም IV	ፊዚዮቴራፒ
የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት	በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር/ቢሮ ብቻ የሚሞላ	
	የሥራው ደረጃ	የሥራው ኮድ
	XVII	
መሥሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ		
በየደረጃው ባሉ ሆስፒታሎች		

II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ ውጤቶችና ተግባራት

2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡-

- የፊዚዮቴራፒ ህክምና፣ የጤና ማበልፀግና በሽታ የመከላከል ትምህርት፣ የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠትና የትምህርትና የስልጠና **ማቴሪያሎችን በማዘጋጀትና ስልጠና በ**መስጠት፣ በፊዚዮቴራፒ ህክምና ዙሪያ የሚደረጉ ምርምና ጥናት በመገምገም እና ክትትል በማድረግ እንዲሁም ምክርና የአቅም ግንባታ በመስጠት የታካሚውን ጤንነት በመመለስ፣ ማህበረሰቡን ተላላፊና ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች በመከላከልና አካል ጉዳተኞችን በማብቃት ወደ ምርታማነት በመመለስ፣ ሃገሪቱን የአካል ጉዳተኝነት መከሰትን በመቀነስና የህብረተሰቡን ጤና እንዲጠበቅ በማድረግ የህክምናው አገልግሎት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ማድረግ ነው።

2.2.የሥራ መደቡ ውጤቶችና ተግባራት

ውጤት **1**፣ የፊዚዮቴራፒ ህክምና መስጠት

- ማንኛውንም የፊዚዮቴራፒ ህክምና ተገልጋይ እንደ እምነቱና ባህሉ መሠረት ተገቢውን ርህራሄ፤ አክብሮትና ጥንቃቄ በማድረግ በተሟላ ሁኔታ ያስተናግዳል፤
- በድንገተኛ ህክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ታካሚዎች ቅድመ ልይታና መረጣ (triage) በማድረግ፣ የህይወት መቀጠል (ABC of life, Basic and Advanced life support) ምርመራና ህክምና ዕርዳታ ይሰጣል።
- የፊዚዮቴራፒ ህክምና የሚያስፈልገዉን ታካሚዉ የህክምና ታሪክ ይወስዳል፣ የታካሚዉን የህክምና መረጃ ያያል፣ አስፈላጊዉን አካላዊ ምርመራ ያደርጋል፣ ዲያግኖስቲክ ምርመራ(ለምሳሌ ራጅ፣ሲቲስካን፣ ኤም አርአይ...ወዘተ) እና የላቦራቶሪ ምርመራዎች እንዳስፈላጊነቱ ያዛል። በዉጤቱ ላይ በመመርኮዝ በሽታውን ይለያል፣ የበሽታውን ዕጣ ፈንታ (prognosis) ሳይንሳዊ ግምት ይሰጣል፣ የሉትን የህክምና አማራጮች ለታካሚው እንዳስፈላጊነቱ ለቤተ-ሰቡ ያስረዳል።
- **አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመድሀኒት አለርጂ በመተንተንና አለመኖሩን በማረጋገጥ ተስማሚ** መድሃኒቶችን ያዛል፣ በተጨማሪም በጅማት፣በጡንቻና በመገጣጠሚያ በመርፌ መድሃኒት ይሰጣል።
- መስመራቸውን ያልሳቱ ስብራቶች እና ቀላል የመገጣጠሚያ ዉልቃቶችን ያስተካክላል፣ ጀሶና ሌሎች የእንቅስቃሴ ማገጃዎችን (Braces) በመጠቀም ያክማል፣ አስፈላጊ ምርመራዎችን በማዘዝ የእንቅስቃሴ ማገጃዎቹ የሚፈቱበትን ጊዜ ይወስናል፣
- በውድድርም ሆነ በልምምድ ጊዜ በስፖርት ላይ የሚደርሱ አደጋና ጉዳቶችን ከህክምና ተቋማት በተጨማሪ እንዳስፈላጊነቱ ስፖርቱ የሚከናወንበት ቦታ በመገኘት ያክማል።
- የነርቭ ማስተላለፍ ብቃት መለካት(nerve conductin study) ምርመራና የጡንቻ የኤሌክትሪካዊ መለኪያ(EMG) በመጠቀምም ምርመራ ያደርጋል፤ ያክማል።
- በልብ፣ በደም ዝዉውርና በመተንፈሻ አካላት የጤና እክሎች(Cardiac, circulation and pulmonary conditions) እንዳስፈላጊነቱ የአካል ብቃት፣ የአተነፋፈስና የልብ ብቃትና የልብ ጫና (physical fitness, aerobic capacity endurance test, cardiopulmonary fitness, cardiac stress